ቁጥር-በአ-2018-3

## የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት የበላይ አመራር ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ

የስብሰባው ቦታ -------------------------**ዋና ዳይሬክተር ቢሮ**

የስብሰባው ቀን --------------------- ሐምሌ 16 ቀን 2018

የስብሰባው ሰዓት--------------------- ከ10፡00-10፡30

| ተ.ቁ | ስም | ኃላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | ዶ/ር ካርታ ካስኬ | ዋና ዳይሬክተር (ሰብሳቢ) | |
| 2 | ዶ/ር አብዮት ብርሃኑ | ም/ዋና ዳይሬክተር | |
| 3 | ወ/ሮ ህይወት በፍቃዱ | የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈፃሚ | |
| 4 | አቶ መኳንንት እያዩ | የኢንስቲትዩቱ ጽ/ቤት ኃላፊ (ጸሀፊ) | |

**አጀንዳ፡- የትምህርትና ስልጠና መመሪያ ማሻሻያ**

የትምህርትና ስልጠና መመሪያው በአፈጻጸም ሂደት ውስጥ የተስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታትና የአፈጻጸም ብቃቱን ለማሻሻል እንዲከለስ በአመራሮች የቀረበው አጀንዳ በስፋት ተወያይቶ የሚከተሉት ውሳኔዎች ተላልፈዋል፡፡

**ውሳኔዎች**

1. በትምህርትና ስልጠና መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 3.3.3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለወጣቶች (ዕድሜያቸው እስከ 35 ዓመት የሆናቸው)፣ ለሴቶች እና ለአካል ጉዳተኞች በራሳቸው ጥረት በውጭ ሀገር የትምህርት ወይም የስልጠና ዕድል ሲያገኙ፣ የተገኘው ዕድል ለመሥሪያ ቤቱ ዓላማ የሚኖረው ፋይዳ ተገምግሞ፣ በከፍተኛ አመራርና በማኔጅመንት ኮሚቴ ከታየና ከጸደቀ በኋላ እንዲፈቀድ ተወስኗል፡፡

2. በራስ ጥረት የሚገኙ ማናቸውም የውጭ ሀገር የትምህርት ወይም የስልጠና ዕድሎች በተመለከተ፣ ለዚሁ ዓላማ ቀደም ብሎ ታቅዶ ከመንግሥት የተፈቀደ በጀት እስከሌለ ድረስ ኢንስቲትዩቱ የትራንስፖርት ወጪን እንደማይሸፍን ተወስኗል።

በአጀንዳው ላይ የተደረገው ውይይት ከተጠናቀቀ በኋላ ከላይ የተጠቀሱት ውሳኔዎች በሙሉ ስምምነት ተላልፈው በሥራ ላይ እንዲውሉ ተወስኗል።